የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ – ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 54
ADDIS ABABA - 7th July 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፹፱ ዓ·ም·
የፌዴራል መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፮፻፳፰

### አዋጅ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፹፱
### የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት
### የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ

የኢትዮጵያ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባደረጉት መራራ ትግል የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት በመረጋገጡ፤

መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳደር ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በሥራ ላይ የሚውለው የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሆኑን የሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፪ (፪) (መ) ስለሚደነግግ፤

የድንጋጌው ተግባራዊነት አጠቃላይ ይዘት ያለው ሆኖ በሁሉም ክልሎች ዘንድ ተፈጻሚነት የሚኖረው የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ማውጣትን ስለሚጠይቅ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 1·60

## CONTENTS

Proclamation No. 89/1997
Federal Rural Land Administration
Proclamation ........................................... Page 628

### PROCLAMATION NO. 89/1997
### RURAL LAND ADMINISTRATION PROCLAMATION OF THE FEDERAL GOVERNMENT OF ETHIOPIA

WHEREAS, as a result of the bitter struggle waged by the Nations, Nationalities and peoples of Ethiopia, it is confirmed in the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia that the right to ownership of land is exculsively vested in the State and in the People;

WHEREAS, Article 52(2)(d) of the Constitution provides that Regional Governments are empowered to administer land and other natural resources in accordance with Federal laws;

WHEREAS, the implementation of said provision calls for the promulgation of a rural land administration law that is of a general scope and consequent identical application to all Regions;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

### *PART ONE*
### *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Federal Rural Land Administration Proclamation NO. 89/1997."

2. *Definitions*

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

፩· "ክልል" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ክልል ሲሆን፡ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ መስተዳድሮችንም ይጨምራል፡

፪· "የገጠር መሬት" ማለት ማዘጋጃ ቤት ከተቋቋመበት ወይም የክልሉ ምክር ቤት አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር ከተማ ብሎ ከሚሰይመው አካባቢ ውጭ ያለ መሬት ነው፡

፫· "የይዞታ መብት" ማለት ማንኛውም አርሶ አደር የገጠር መሬት ለግብርና ተግባር ለማዋል፡ ለማከራየትና ይዞታው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ለቤተሰቡ አባል ለማውረስ የሚኖረው መብት ሲሆን፡ በመሬቱ ላይ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት ማፍራትንና ይኸንኑም መሸጥ፡ መለወጥና ማውረስን ይጨምራል፡

፬· "የይዞታ ሽግሽግ" ማለት የይዞታ መብት ፍትሐዊ በሆነና በተመጣጠነ መንገድ እንዲዳረስና አርሶ አደሮች በጋራ የሚጠቀሙበት መሬት ተለይቶ እንዲከለል ለማድረግ በነዋሪው ሕዝብ ውሳኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከናወን የገጠር መሬት ድልደላ ተግባር ነው፡

፭· "የቤተሰብ አባል" ማለት የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ ገቢ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖር ማንኛውም ሰው ነው፡

፮· "የመሬት አስተዳደር" ማለት የይዞታ መብት አወሳሰንና የይዞታ ሽግሽግ አፈጻጸም ነው።

፫· <u>የፆታ አገላለጽ</u>

ከዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የመሬት አስተዳደርን የሚመለከቱ አጠቃላይ ድንጋጌዎች</u>

፬· <u>መሠረተ ሃሳብ</u>

መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው።

፭· <u>የመሬት አስተዳደር ስለሚመራበት ሁኔታ</u>

፩· ማንኛውም ክልል የገጠር መሬት የሚያስተዳድረው በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት አጠቃላይ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል።

፪· ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ አፈጻጸም እያንዳንዱ የክልል ምክር ቤት የመሬት አስተዳደር ሕግ ያወጣል።

፫· የክልል የመሬት አስተዳደር ሕግ የአካባቢ ጥበቃን አስመልክቶ ከወጡ ሕጎች ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣመ እና የፌዴራል መንግሥት የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲን ያገናዘበ መሆን አለበት።

፬· የክልል የመሬት አስተዳደር ሕግ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር እንዲሁም የይዞታ መብትን በማስተላለፍና በማውረስ ረገድ የሴቶችን የእኩልነት መብት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት።

፮· <u>የመሬት አስተዳደር ሕግ ይዘት</u>

የየክልሉ ምክር ቤት የሚያወጣው የመሬት አስተዳደር ሕግ፤

፩· ከፆታ አድልዎ የጸዳ የይዞታ መብት ለአርሶ አደሩና ለዘላኖች በነፃ ማስገኘትን የሚያረጋግጥ እንዲሁም በክልሉ ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት በክልሉ አጠቃላይ ወይም በከፊል በሚደረግ የመሬት ሽግሽግ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማንኛውም ምክንያት ከይዞታ መብት አለመነቀልና አለመፈናቀልን የሚያስከብር፤

"Region" means a Region specified, under Article 47 of the Constitution, as a member of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa Administrations;

2) "rural land" means all land outside the boundaries of a municipality or outside an area which the respective Regional Council, in consultation with the appropriate body, designates as a town;

3) "holding right" means the right any peasant shall have to use rural land for agricultural purposes as well as to lease and, while the right remains in effect, bequeath it to his family member; and includes the right to acquire property thereon, by his labour or capital, and to sell, exchange and bequeath same;

4) "distribution of holdings" means a rural land allocation measure taken at intervals, upon decision of the community, with a view to assigning holding rights in a fair and proportionate manner as well as to demarcating land for communal use by peasants;

5) "family member" means anyone permanently living with a person having holding rights, by way of sharing the means of livelihood of the latter;

6) "land administration" means the assignment of holding rights and the execution of distribution of holdings.

3. *General Reference*

The provisions of this Proclamation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## PART TWO
## *General Provisions on Land Administration*

4. *Principle*

Land is a common property of the Nations, Nationalities and Peoples of Ethiopia shall not be subject to sale or to other means of exchange.

5. *Conditions of Land Administration*

1) Any Region shall administer rural land in accordance with the general provisions of this Proclamation.
2) For purposes of implementation of the provisions of sub-Article (1) of this Article, each Regional Council shall enact a law on land administration.
3) The land administration law of a Region shall be in conformity with the provisions of laws on environmental protection and shall observe the Federal land utilization policies.
4) The land administration law of a Region shall confirm the equal rights of women in respect of the use, administration and control of land as well as in respect of transferring and bequeathing holding rights.

6 *Contents of a Land Administration Law*

A land administration law enacted by each Regional Council, shall:

1) ensure free assignment of holding rights both to peasants and nomads, without differentiation of the sexes; as well as secure against eviction and displacement from holdings on any grounds other than total or partial distribution of holdings effected pursuant to decision by the Regional Council,

፪· እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ለአርሶ አደሮችና ለዘላኖች በግብርና ሥራ ለመተዳደሪያ በቂ የሆነ የይዞታ መብት የሚያስገኝ፣

፫· ሴቶች በይዞታ መብታቸው ላይ ሌሎችን ቀጥረው ወይም በሌላ አኳኋን ተስማምተው ሊያሠሩ እንደሚችሉ የሚፈቅድ፣

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰውን መብት ለአካለ መጠን ላልደረሱ ዕጓለ ማውታን፣ ለአቅመ ደካሞች እና ለመሳሰሉትም የሚፈቅድ፣

፭· ለይዞታ ባለመብትነት ብቁ የሚያደርጉ እንደቤተሰብ ኃላፊነት፣ አዲስ ጐጆ ወጪነት ያሉ መስፈርቶችን እንዲሁም እንደቤተሰብ አባላት ብዛት ያሉ የመሬት ፍላጐት መጠን ተጨባጭ መመዘኛዎችን በመከተል የይዞታ መብቱ የሚሰጥበትን ስፋትና ጥበት በቅደም ተከተል የሚወስን፣

፮· ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ፣ ለግጦሽ፣ ለደን፣ ለማኅበራዊ አገልግሎትና ለመሳሰለው የጋራ መጠቀሚያ የሚውል መሬት አከላለል እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ እና በሕዝብ ተሳትፎ እንደሚወሰን የሚደነግግ፣

፯· የይዞታ ሽግሽግ ሲከናወን ሕጋዊ የሆኑ ነባር ባለይዞታዎች በጉልበታቸው ወይም በገንዘባቸው ሲያለሙ ከቆዩት መሬት ውስጥ በተቻለ መጠን ሽግሽጉ የሚፈቅድላቸውን ያህል መሬት በእጃቸው እንዲቆይ ዕድል የሚሰጥ፣

፰· በይዞታ ሽግሽግ አፈጻጸም የይዞታ መብት በሚለዋወጥበት ጊዜ የቀድሞው ሕጋዊ ባለይዞታ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ላከናወነው መሬቱን ራሱን የማልማት ሥራ ተገቢውን ካሳ ከአዲሱ ባለይዞታ እንዲያገኝ የሚያስችል፣

፱· በይዞታ ሽግሽግ አፈጻጸም የይዞታ መብት ሲለዋወጥ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ሲቋረጥ በመሬቱ ላይ የተፈራውን ከመሬቱ ሊነጠል የማይችል ቋሚ ንብረት ወይም ሀብት የማንሳት ወይም ለዚሁ የካሳ ክፍያ ወይም አላባ የመጠየቅን መብት የሚያስጠብቅ፣

፲· የይዞታ መብት የሚሰጥበትንና የይዞታ ሽግሽግ የሚከናወንበትን ግልጽና ፍትሐዊ የሆነ እንዲሁም አርሶ አደሩን በተለይም ሴቶችን የሚያሳትፍ የአፈጻጸም ሥርዓት የሚዘረጋ፣

፲፩· በይዞታ መብት እና በይዞታ ሽግሽግ ጉዳይ ለሚነሱ ቅሬታዎች የአፈታት ሥርዓት የሚያበጅ፣

፲፪· ከዚህ አዋጅ ጋር የማይቃረኑ ሌሎች አጠቃላይ ወይም እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ አስፈላጊ ሆነው የሚገኙ የተለዩ ጉዳዮችን የሚደነግግ

ይዘት ያለው መሆን አለበት።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

ስለገጠር መሬት ይዞታ ክፍያዎች

፩· በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፺፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፲) በተደነገገው መሠረት፣ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያ መጠን በክልል መስተዳድሮች የሚወሰንና የሚሰበሰብ ይሆናል።

፪· የክልል ምክር ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የክፍያ መጠን ሲወስኑ ተመጣጣኝነቱን ማረጋገጥ አለባቸው።

2) assign holding rights sufficient for subsistence, both to peasants and nomads, subject to the particular conditions of the locality;

3) allow women to use hired labour on their holdings or to, otherwise, make agreements thereto;

4) permit the right referred to under sub-Article (3) of this Article, to orphans not having attained majority, the physically weak and to similar others;

5) fix criteria, such as family responsibility and formation of a new marriage, for qualification to a holding right; as well as set out standards, in a descending order of priority based on family-size and such other objective factors of assessment of land demand, for determination of the extent to which holding rights would be assigned;

6) provide that demarcation of land for house-building, grazing, forests, social services and such other communal use shall be carried out in accordance with the particular conditions of the locality and through communal participation;

7) with respect to former holders of lawful standing and where distribution of holdings is effected, allow for an opportunity to retain, to the extent the distribution would permit, portions of the land they have been improving upon their labour or capital;

8) where a holding right changes hands under distribution of holdings, ensure payment of due compensation, by the new holder, to a previous and lawful holder for improvements he had made on the land by his labour or capital;

9) where a holding right changes hands under distribution of holdings or terminate on various grounds, guarantee the right to remove permanent work builts, or tree-crops cultivated, on the land or to claim payment of compensation thereon or collection of the fruits thereof;

10) lay down a system based upon transparency, fairness as well as the participation of peasants, especially of women, for purposes of assigning holding rights and carrying out distribution of holdings;

11) provide for a grievance procedure on matters pertaining to holding rights and distribution of holdings;

12) make provisions, not inconsistent with this Proclamation, for other general or particular matters as found necessary under the peculiar circumstances of the locality;

## PART THREE

## *Miscellaneous Provisions*

7. *Payments on Rural Land Holdings*

1) Persuant to the provisions of sub-Articles (2) and (10) of Article 97 of the constitution, Regional Governments shall determine the rate of, and collect, land-use-fees and royalties on the use of forest resources.

2) In fixing rates under sub-Article (1) of this Article, Regional Councils shall ensure the proportionality thereof.

፰· <u>ስለክልል የመሬት አስተዳደር ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

የመሬት አስተዳደርን በተመለከተ በማንኛውም የክልል ምክር ቤት የወጣ ሕግ ከዚህ አዋጅ ጋር የማይቃረን እስከሆነ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፱· <u>ከሌሎች ሕጎች ጋር ስላለው ግንኙነት</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውንም ነባር ሕጎች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፲· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

8. *Applicability of Land Administration Laws of Regions*

A land administration law heretofore enacted by any Regional Council shall be applicable insofar as it is not inconsistent with this Proclamation.

9. *Relation with Other Laws*

Any previous laws inconsistent with this Proclamation shall not be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

10. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 7th day of July, 1997.

Done at Addis Ababa, this 7th day of July, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE